በአማራ ብሔራዊክልላዊመንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/1452/18

ቀን፡ 07/12/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ገቢዎች ቢሮ

ባሕር ዳር

ጉዳዩ፡ **የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም መሠረት፣ ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ፣ እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን ለፍትሕ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንደሚገባው ተደንግጓል።

በዚህ መሠረት የገቢዎች ቢሮ በታክስ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን መርምሮ ለመወሰን የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 005/2011 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወንለት መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትሕ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 005/2011 ዓ.ም በመመርመር መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 149/2018 ዓ.ም ሆኖ በሥራ ላይ እንዲውል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ1ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

ገረመው እሸቱ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት (ያለ አባሪ)
- ለፍትሓብሔርና /ሕግ ጉዳይ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
- ፍትሕ ቢሮ

Tl.No ☎ 058 222 0794/793 /058 226 52 92 ✉ 995

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የገቢዎች ቢሮ

በታክስ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን መርምሮ ለመወሰን የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር አገቢ 149/2018 ዓ.ም

የአማራ ገቢዎች ቢሮ

2011 ዓ.ም

ባህር ዳር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ግጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

በአዲሱ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ዓ.ም እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 እንዲሁም አዋጆችን ተከትሎ ከወጡ ደንቦች ጋር የተጣጣመ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 54 እና 55 መሰረት ታክስ ከፋዮች ከታክስ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ሲያቀርቡ ቅሬታቸውን በመቀበልና በማጣራት ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንገስት ገቢዎች ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 61(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥታል።

ክፍል አንድ
የወል ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

1.1 ይህ መመሪያ "ታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን መርምሮ ለመወሰን የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር- 149/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

2.1 "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ እና በየደረጃው በክልሉ የሚገኝ የገቢ ተቃመ ማለት ነው።

2.2 "ኃላፊ" ማለት የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው ወይም በየደረጃው የሚገን የገቢ ኃላፊ ነ።

2.3 "የስራ ሂደት" ማለት በቢሮው እና በየደረጃዉ በሚገኙ ገቢ መምሪያዎች እና ጽ/ቤቶች የተቋቋመ የደንበኞች አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት ነው።

2.4 "የንግድ ስራ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 2 ከንዑስ አንቀጽ 2-5 የተገለጸዉን ትርጉም የያዘ ሲሆን በተከታታይ ወይም ለአጭር ጊዜ ለትርፍ የሚከናወን ማንኛዉም የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የሙያ ወይም ቮኬሽናል ስራ ሲሆን ተቀጣሪ ለቀጣሪዉ የሚሰጠዉን አገልግሎት ወይም ቤት ማከራየትን አይጨምርም፣

2.5 "ታክስ ከፋይ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 41 መሰረት ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ሰዉ ነዉ።

2.6 "ቅሬታ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 54 እና 55 መሰረት በጽሁፍ የሚያቀርብ ጥያቄ ነዉ።

2.7 "ቅሬታ አጣሪ ቡድን" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 54 መሰረት በደንበኞች አገልግሎት ዋና የስራ ሂደት ስር ለስራው አመችነት ሲባል ከታክስ ጋር በተያያዘ ከታክስ ከፋዮች የሚቀርቡ ቅሬታዉችን ተቀብሎ በነፃነት በመመርመር የዉሳኔ ሀሳብ ለኃላፊ የሚያቀርብ የሙያተኞች ቡድን ነዉ።

2.8 "የታክስ ውሳኔ ሀሳብ" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 55(1) መሰረት በአግባቡ የቀረቡ ቅሬታዎችን በነጻነት በመመርመር ለኃላፊ የሚቀርበውን ውሳኔ ሀሳብ ማለት ነው።

2.9 "የታክስ ውሳኔ" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 55(4) መሰረት በቅሬታ አጣሪ ቡድን የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ በኃላፊ የሚሰጥ የመጨረሻ ሻኔ ነ።

2.10 "ከአቅም በላይ የሆነ ምክኒያት" ማለት ታክስ ከፋዩ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች የሚከሰቱ፤ በተወሰነ አካባቢ የተነሳ ወይም የተፈጠረ ጦርነት፣ የመድን ሽፋን የሌላቸውና በንግድ ስራው ላይ ጫና የሚፈጥር (እንደ ዝርፊያ፣ ጉርፍ፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች)፣ የታክስ ከፋዩን ጽኑ ህመም ወይም ሞት ሲያጋጥም፡ ወይም የታክስ እንደራሴ የሌለዉ ጽኑ ህመም ወይም ሞት ሲያጋጥም እና ታክስ ከፋዩ ያለበትን የግብር፣ ታክስ ወይም ቀረጥ የታክስ ዕዳ መክፈል አለመቻል

2.11 በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጎች እንደአግባብነቱ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 እና የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፣

3. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው የታክስ ቅሬታ በሚያቀርቡ ታክስ ከፋዮች እና አገልግሎት በሚሰጡ ሰራተኞችና ሀላፊዎች ላይ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የታክስ ቅሬታ የማየት ሥልጣን፣ የቅሬታ ሰሚ ቡድን አደረጃጀት፣ የቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ</u>

4. **<u>ቅሬታ የማየት ስልጣን፣</u>**

4.1 በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 54 መሰረት በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ የቀረበዉን ቅሬታ ተቀብሎ በነፃነት በመመርመር የዉሳኔ ሀሳብ ለሃላፊ ማቅረብ ያለበት የስራ ክፍል እንደሚቋቋም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገ በመሆኑ፣

4.2 በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4.1 በተደነገገው መሰረት የተደራጀው የሥራ ክፍል የደንበኞች አገልግሎት ዋናየሥራ ሂደት ወይም የሥራ ሂደቱ በሌለበት በገቢ ተቋሙ የሚቋቋመው የቅሬታ አጣሪ ቡድን ነው።

5. በሁሉም የታችኛዉ የቢሮው አስተደደር እርከን በሚገኙ ጽ/ቤቶች ታክስ ለመወሰንና ለመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸዉ ሲሆን ደንበኛዉ በታክስ ጉዳዮች ባለመስማማት ቅሬታዉን ታክስ ለሚከፍልበት ገቢ ጽ/ቤት አቅርቦ ምላሽ የማግኘት መብት ያለዉ ሲሆን ነገር ግን ታክስ ከፋዩ በተሰጠዉ ምላሽ ካልተስማማ ደረጃዉን ጠብቆ ለቢሮው ሲያቀርብ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት ቢሮው የቀረቡለትን ቅሬታ የይግባኝ ጊዜዉ ከማለፉ ወይም በይግባኝ ኮሚሽን ዉሳኔ አለመሰጠቱን በማረጋገጥ እና በታችኛዉ አስተዳደር እርከን የተሰጠዉን ዉሳኔ በተቀመጠዉ ህግ መሰረት መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማጣራት ተገቢዉን ምላሽ መስጠት እንዳለበት በመደንገጉ።

6. **<u>የቅሬታ ሰሚ ቡድን አደረጃጀት</u>**

6.1 በ3ቱ ሜትሮ ፖሊታንት ከተሞች /ባህር ዳር፣ ጎንደር እና ደሴ/ ከሚኖራቸዉ የግብር ከፋይ ቁጥር አንፃር ከደንበኞች የሚቀርብን የታክስ ቅሬታ በተፋጠነ ሁኔታ

ለማሰተናገድ እንዲቻል የሙያተኞች ቁጥር መሰረት በማድረግ 3 አባላት ያሉት ከአንድ ኮሚቴ በላይ የቅሬታ አጣሪ ቡድን ሊያደራጁ ይችላሉ።

6.2 በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.1 የተገለጸዉ ቢኖርም ሁለቱ ቡድኖች የሚደራጁ ከሆነ ከቀረበላቸዉ ቅሬታዎች ዉስጥ በጋራ ማየት አለብን ብለዉ የሚያምኑትን በመምረጥ በጋራ ሊያዩ ይችላሉ።

6.3 በሁለተኛ ደረጃ ከተሞች ከደንበኞች የሚቀርብን የታክስ ቅሬታ ለማሰተናገድ እንዲቻል 3 አባላት ያሉት አንድ ቡድን የሚዋቀር ይሆናል፤

6.4 በሁሉም የቅሬታ አጣሪ የቡድን አደረጃጀቶች ከአባላቱ ዉስጥ በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች አንዱ አባል ባይኖር ከሂደቱ ሰራተኞች መካከል በስነ ምግባሩና በአፈፃፀም የተሻለዉን በመምረጥ አቤቱታዉ መታየት አለበት።

6.5. በአንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 4.2 በተደነገገው መሠረት በቀበሌ ገቢ ማዕከላት የደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት በማይኖርበት ሁኔታ የሚቀርቡ የታክስ ቅሬታዎችን አጣርቶ መወሰን የሚችለው የገቢ አሰባሰብና ክትትል ዋና ስራ ሂደት ባለሙያዎች ይሆናሉ።

6.6 በሌሎች ከተሞችና ወረዳዎች እንዲሁም ቀጣይ በሚፈጠሩ ሌሎች አደረጃጀቶች የወረዳ ደረጃ የሚኖራቸዉ የቀበሌ ገቢ ጽ/ቤቶች ቢኖሩ ከስራ ሂደቱ ሙያተኞች ቁጥር አንፃር ቅሬታ ተቀብለዉ ምላሽ የሚሰጡ 3 አባላት ያሉት ወይም እንዳስፈላጊነቱ የሰራተኛ ቁጥር የሚጨምር ሲሆን ከዚያም በላይ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን ሊቋቋም ይችላል፤

7. <u>የታክስ ቅሬታ አቀባበልና የማጣራት ተግባር:-</u>

በታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ አቀራረብና የማጣራት ተግባራት

1) በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በታክስ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ታክስ ከፋይ የታክስ ዉሳኔዉ በደረሰዉ በ 21 ቀን ዉስጥ የቅሬታ ማመልከቻዉ የቀረበ መሆኑን ማረጋገጥ ፣

2) በቀረበዉ የታክስ ዉሳኔ የቅሬታ ማመልከቻ በአግባቡ አልቀረበም ብሎ ካመነ ቅሬታዉን አለመቀበል የሚችል ሲሆን ቅሬታዉን ያልተቀበለበትን ምክንያት ለቅሬታ አቅራቢዉ ወዲያዉኑ በጽሁፍ ምላሽ ይሰጣል፣

3) የቀረበዉን አቤቱታ ከድርጅቱ ገቢ ጋር ያለዉን ተዛምዶ መመርመር፣

4) የቀረበ ቅሬታ በሚመረምርበት ጊዜ ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰራተኞች ወይም ኃላፊዎች በአካል አስጠርቶ ወይም በጽሁፍ ማብራሪያ እንዲሰጡ መጠየቅ፣

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7.4 መሰረት በሚጣራዉ ቅሬታ ላይ በአካል ወይም በጽሁፍ ምላሽ እንዲሰጥ የተጠየቀ አካል እንደጉዳዩ ዉስብስብነት ከአንድ ቀን እስከ 5 ቀን ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፣ ነገር ግን የሚጣራው ቅሬታ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልግ ሆኖ ሲገኝ ለጽ/ቤት ኃላፊዎች በማሳወቅ ከ10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ተጠቅሞ ማጣራት አለበት ሆኖም የቅሬታው ውስብስብነት ታይቶ እንደአስፈላጊነ የጽ/ቤት ኃላፊው በ180 ቀን ውስጥ ቅሬታው ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥ መፍቀድ ይችላል።

6) ቅሬታ አቅራቢው የቅሬታ መልስ ሊሰጥ በሚገባበት ጊዜ መልስ ካልተሰጠው በቀጥታ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል።

7) የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ የሚቆጠረዉ የታክስ ማስታወቂያዉ ለግብር ከፋዩ ከደረሰበት ወይም በተለያዩ ሁኔታዎች ማለትም ከድርጅቱ ከተለጠፈ፣ በህዝብ መገናኛ ዘዴዎች እንዲያዉቀዉ ከተደረገ፣ ለህጋዊ ወኪሉ ወይም በድርጅቱ ዉስጥ ሀላፊነት ወስዶ እየሰራ ለሚገኝ አካል የታክስ ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 21 ቀን ዉስጥ ወይም በአሳማኝ ሁኔታ ተጨማሪ የቅሬታ ማቅረቢ ጊዜ የተሰጠዉ ከሆነ በተጨማሪ በተሰጠው በ10 ቀን ዉስጥ መቅረብ አለበት።

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተደነገገው ቢኖርም የቅሬታ ማቅረቢያው የመጨረሻ ቀናት እሁድ ወይም ብሔራዊ በዓል ቀን ተከታታይ ከሆነ በሚቀጥሉት ቀናት ማቅረብ ይችላል።

9) በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በቢሮው እና የታችኛው እርከን በህጉና በአግባቡ ያልተፈቱ ቅሬታዎች ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ ወይም በይግባኝ ኮሚሽን ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት ለቢሮው ቅሬታ ማቅረብ ይችላል።

10) የቅሬታ አጣሪ ቡድን የቀረበለትን ቅሬታ ሲመረምር /ሲያጣራ/ ይንግድ ድርጅቱን በአካል ያያል።አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችንና ማስረጃዎችን አቅርቦ ያያል ወይም እንዲቀርብለት የሚመለከተዉን ያዝዛል፣ ቅሬታ አቅራቢዉ ቅሬታዉን ቀርቦ እንዲያስረዳ ያደርጋል፣ ምስክሮችንና ባለሙያዎችን ጠርቶ እንዲያስረዱ ይጠይቃል ወይም የቅሬታ መነሻ የሆነዉን ወይም ዉሳኔ የሰጠዉን ባለሙያ ወይም የስራ ሀላፊ በጽሁፍ ወይም በግንባር ቀርበዉ እንዲያስረዱ ያደርጋል፣

11) የቅሬታ አጣሪ ቡድኑ የቀረበዉን ቅሬታ ሲመረምር በታክስ ስሌት የተመለከተዉ የታክስ መጠን ሊጨምር ይገባዋል የሚል እምነት ሲኖረዉ የታክስ ስሌቱ ለሚመለከተዉ አካል እንደገና እንዲታይ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ለሀላፊዉ የዉሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

12) የሚቀርቡ የታክስ ዉሳኔ ቅሬታዎችን ከመቀበልና አፋጣኝ ምላሽ ከመስጠት በተጨማሪ ቅሬታዎችን ከምንጩ ለማደረቅ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መነሻ መሰረት በማድረግ የትንተና ሪፖርት ያዘጋጃል፣ በህግና በአሰራር ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸዉን በመቀመር ለሀላፊ የዉሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

13) የቀረበው ጉዳይ ታክስ መክፈል ሳይኖርባቸው ያለአግባብ ታክስ የተወሰነባቸው መደበኛ ገቢ የሌላቸዉ የጎብረተሰብ ክፍሎች ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተወሰነባቸውን ታክስ የመክፈል አቅም የሌላቸዉን ታክስ ከፋዮች ጉዳይ ሲሆን በትክክል መክፈል የማይገባቸው ወይም የማይችሉ መሆኑን ምክንያቶችን የማጣራትና ከታክስ ህጎች አንፃር በማየት የዉሳኔ ሀሳብ ለኃላፊ ያቀርባል፣

14) የቅሬታ አጣሪ ቡድን አባላቱ ቅሬታዎችን በጋራ በመመርመርና የራሳቸውን ግንዛቤ ከታክስ ህጉ አንፃር አይቶ በመጨመር በተጨባጭ ማሰረጃዎች ላይ በመመስረት የቀረበውን የታክስ ቅሬታ በመቀነስ ወይም በማፅናት ወይም እንዲሻሻል የውሳኔ ሃሳብ ለኃላፊ ያቀርባል፣

15) ታክስ ከፋዩ በተሰጠዉ የታክስ ቅሬታ መልስ ባለመስማማት የታክስ ይግባኝ ቢጠይቅ ስለተሰጠዉ የውሳኔ ሃሳብ ለታክስ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ወይም ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ለፍ/ቤት ማስረዳት ያለበት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 59 መሰረት ታክስ ከፋዩ ነው።

16) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 15 እንደተጠበቀ ሆኖ ለቀረበ ይግባኝ ጥያቄ ውሳኔ ሰጭ አካላት ገቢ ተቋሙን በታክስ ውሳኔው ላይ እንዲሰረዳ የሚጠይቁ ከሆነ ግን የደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ቅሬታውን አጣርተው የውሳኔ ሀሳብ ለሀላፊ ካቀረቡ የቡድኑ አባላት መካከል አንዱ ወይም እንደ ጉዳዩ አሰፈላጊነት የገቢ ጽ/ቤቱ ኃላፊ ጋር በመመካከር ጉዳዩን ሊያስረዳ ይችላል ብሎ ያመነዉን ከሌሎች የሥራ ሂደቶች ሙያተኛ ወይም የስራ ኃላፊ ሊወክል ይችላል፣

8. <u>የቅሬታ አጣሪ ቡድን ተግባርና ኃላፊነት ፣</u>

1) የቀረቡ ቅሬታዎችን አጣርቶ ዉሳኔ ለመስጠት አስፈላጊዉን ቅድመ ዝግጅት ማድረግና ቅደም ተከተል እንዲይዙ ማድረግ፣

2) ከቀረቡ ቅሬታዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን መረጃዎች በማሰባሰብ አደራጅቶ በመያዝ ማብራሪያዎችን መስጠት፣

3) ቅሬታ አቅራቢዉ ተጨማሪ መረጃ ለማሟላት የሚያስፈልገዉ ከሆነ በማረጋገጥ ተጨማሪ ጊዜ ቢበዛ እስከ 5 ቀን መስጠት፡፡ ስላቀረበዉ ቅሬታም ባጭሩ በአካል ቀርቦ / በህጋዊ ወኪሉ/ እንዲያስተረዳ ማድረግ፣

4) የቅሬታ ምላሽ ለመስጠት ከሶስተኛ ወገን ተጨማሪ መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስፈልግ ከሆነ መረጃ ማሰባሰብና አጣርቶ በወቅቱ ምላሽ መስጠት፣

5) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቅሬታዉን ለማጣራት ከመረጃ ጋር ግንኙነት ያላቸዉን አካላት በመጥራት እንዲያስረዱ ማድረግ፣ በተሰበሰበዉ መረጃ በተገኘዉ ግበዓት መሰረት ዉሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀት ለኃላፊዉ ማቅረብ፣

6) የቅሬታ አጣሪ ቡድን አባላት በታክስ ህጎች መሰረት በመወያየት ተግባብቶ ምላሽ መስጠት፣

7) የቅሬታ አጣሪ ቡድን በህጉና በማስረጃዎች ላይ ተመስርቶ ግልጽና ፍትሃዊ የዉሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣

8) የቅሬታ አጣሪ ቡድን አባላት የቀረበለትን ቅሬታና ተያያዥ ሰነዶች ሚስጢራዊነት መጠበቅ፣ መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝ፣ ሪፖርት አደራጅቶ ማቅረብ፣

9) ለኃላፊዉ ወይም እርሱ ለሚወክለው ሰው የቀረቡ የቅሬታ የውሳኔ ሀሳቦች ኃላፊው በበቂ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ እንደገና ታይተዉ መቅረብ አለባቸዉ ብሎ ሲመራዉ የመረጃዎችን ትክክልኛነት ከታክስ ህጉ አንፃር በድጋሚ በማገናዘብ የዉሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣

10) ኃላፊ በቅሬታ አጣሪ ቡድኑ ቡድኑ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ አይቶ ቡድኑ ያላየው ጉዳይ መኖሩን ከታክስ ህጉ አንጻር አገናዝቦ እንደገና እንዲታይ ለቅሬታ አጣሪ ቡድኑ የመለሰውን ቡድኑ ተቀብሎ አላሻሽልም ካለ የጽ/ቤጽ ኃላፊው በማጽናት ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

11) የቅሬታ አጣሪ ቡድን ለቀረበ የታክስ ቅሬታ በታክስ ህጉ መሰረት በወቅቱ አጣርቶ የውሳኔ ኃሳብ ለኃላፊ ያቀርባል፡፡

12) የቅሬታ አጣሪ ቡድኑ ለሚያከናውነዉ ተግባር ከህግ ዉጭ ተፈጽሞ ቢገኝ የተናጠልም ሆነ የጋራ ተጠያቂነት አለበት፣

13) የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን አባላት ከታክስ ከፋዮች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመደበኛ ስራቸዉ አካል አድርገዉ በመቁጠር ቅሬታዎችን ተቀብሎ በማጣራት በኃላፊዎች ውሳኔ እንዲሰጣቸው በመከታተል ውሳኔ ያገኙትን ታክስ ከፋዮች አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ የማድረግ ሀላፊነት አለባቸዉ፣

14) የታክስ ከፋዮች ቅሬታ ምላሽ ለመስጠት ከአንድ የሥራ ቀን በላይ የሆነ ጊዜ የማይጠይቅ ሆኖ ሲገኝ ወዲያዉኑ ምላሽ እንዲገኝ ይደረጋል፡፡

15) በየደረጃው በሚገኝ የገቢ ተቋም የሚቀርበው ቅሬታ ከአንድ የሥራ ቀን በላይ የሆነ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ ቅሬታዉን በመመዝገብ ቀጠሮ ይሰጣል፣ በታክስ ከፋዩ የቀረቡ ቅሬታዎች በታክስ አስተዳር አዋጅ 241/2008 አንቀጽ 55/7 በተገለፀው ድንጋጌ መሰረት ምላሽ ይሰጣል፡፡ታክስ ከፋዩ ቀጠሮ ሲሰጠው ለተቀጠረበት ጊዜ መተማመኛ ወይም የቀጠሮ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

16) ቅሬታ ያቀረበው ታክስ ከፋይ በተቀጠረበት ጊዜ ሲገኝ ወይም ወዲያውኑ እንዲታይ ሲወሰን ጉዳዩ ወዲያውኑ አልቆ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡ በተቀጠረበት ጊዜ ውሳኔ ያልተሰጠው ታክስ ከፋይ በተሰጠው የቀጠሮ መተማመኛ መሠረት በባለሙያዉ ጥፋት ላባከነው ጊዜ ባለሙያዎቹ ተጠያቂ ሆነው የባለጉዳዩ አቤቱታ ወዲያውኑ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

17) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16 የተጠቀሰው ቢኖርም በኃላፊው የመጨረሻ ውሳኔ ካልተሰጠው ደንበኛው ለተጨማሪ ወጭና ጊዜ እንዳይዳረግ ቀጠሮ ከተያዘለት ቀን በፊት ደንበኛው በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

18) ቅሬታ አጣሪዉ ቡድን በዉሳኔ ሀሳብ አሰጣጥ ልዩነት ከተፈጠረ በአብላጫ ድምጽ የተደገፈዉ የውሳኔ ሃሳብ የቡድኑ የውሳኔ ሃሳብ ይሆናል፤

19) በውሳኔው ሀሳብ ማቅረቢያዉ ቅጽ ላይ የቡድን አባላቱ ፊርማ ይቀመጣል፡፡

20) የቀረበዉ ቅሬታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14 መሰረት ምላሽ የሚሰጥ ቢሆንም ምላሽ የሚሰጥበት ጊዜን በተመለከተ ቅሬታው የሚታይበት በገቢ ተቋሙ ቅሬታ አጣሪ ቡድን ኃለፊ እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን ይሆናል፣

21) ቅሬታ ያቀረበዉ ታክስ ከፋይ ባቀረበዉ ቅሬታ በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳና አሉኝ የሚላቸዉን ማስረጃዎች እንዲያቀርብ በተጨባጭ ጥሪ የደረሰዉ መሆኑን ያረጋግጣል፣

22) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 21 የተገለጸዉ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጥሪ ተደርጎለት ወይም እንዲያዉቀዉ ተደርጎ በዕለቱ ያልቀረበ ቅሬታ አቅራቢ ጉዳዩ በሌለበት ዉሳኔ ሊሰጥ ይችላል ነገር ግን ቅሬታ አቅራቢው መቅረብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክናየት መሆኑ ከታመነበት ለተጨማሪ አንድ ጊዜ ጥሪ በማድረግ ውሳኔ መስጥት ይቻላል ። ሆኖም ጥሪዉን ሰምቶ ያልቀረበ ከሆነ በዉሳኔዉ አስተያት ላይ መመላከት አለበት፣

23) በዚህ አንቀጽ ስር የተዘረዘሩት ተግባራት የሰዉ ሀይል ቁጥር ባለባቸዉ ወረዳ፣ ከተሞችና ቀበሌ አስተዳደሮች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በዞንና በክልል ደረጃ ይህ አደረጃጀት ባይኖርም የሚቀርቡ የታክስ ቅሬታዎችን ደረጃቸዉን ጠብቀዉና የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜያቸዉ ያላለፈ እና በታክስ ይግባኝ ሰሚ ቀርቦ ምላሽ ያልተሰጠበት መሆኑን በማረጋገጥ በከተሞችና በወረዳዎች የተሰጡ ዉሳኔዎች የታክስ ህጉን ተከትለዉ ዉሳኔ ያገኙ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሀላፊዉ ጋር በመነጋገር ወይም በማሳወቅ በስራ ሂደቱ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ፣ ነገር ግን በስራ ሂደቱ የማያልቁና የበላይ ሀላፊዉን ዉሳኔ የሚጠይቁ ናቸዉ ተብለዉ የሚታመንባቸዉን ቅሬታዎች ከገቢ ግብር አዋጁ እና ከታክስ አስተዳደር አዋጁ እንዲሁም ስራ ላይ በዋሉ መመሪያና አሰራሮች መሰረት ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ሌሎች አማራጮች በመተንተን የዉሳኔ ሀሳብ ለሃላፊ ያቀርባል።

24) በየደረጃው በተሰጠ የታክስ ቅሬታ ውሳኔ የማይስማሙ ታክስ ከፋዮች ይግባኝ ከጠየቁ በታክስ አስተዳድር አዋጅ 241/2008 በአንቀጽ 56 ስር በተዘረዘሩ ድንጋጌዎች እና በአንቀጽ 87/1 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ጥያቄው መቅረቡን በማረጋገጥ ይግባኙን ለቅሬታ አቅራቢው ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ /ኮሚሽን/ እንዲያቀርብ ይሰጣል።

25) በክልል ደረጃ ቀርቦ ውሳኔ የተሰጠው ቅሬታ የተሰጠው ውሳኔ በትክክለኛ መረጃ ተመስርቶ የታየልን አይደለም በሚል ቅሬታ አቅራቢው ከጠየቀና ቢሮው ካመነበት

በተጨማሪ 21 ቀናት ውስጥ ለአንድ ጊዜ ብቻ እንደገና ቅሬታው እንዲታይለት ሊፈቅድ ይችላል።

9. የቅሬታ አጣሪ ቡድን የዉሳኔ ሀሳብ አቀራረብ ስርዓት፣

9.1 ከቅሬታ አጣሪ ቡድን አባላት ዉስጥ ሰብሳቢዉን ጨምሮ ሁለት ሶስተኛዉ ከተሟላ ምልዓተ ጉባኤዉ እንደተሟላ ይቆጠራል፣

9.2 በታክስ ዉሳኔ ሀሳብ አቀራረብ እኩል ድምጽ የሚሰጥ ከሆነ ሃላፊዉ የሚደግፈዉ የቅሬታ ሰሚዉ ዉሳኔ ሀሳብ ይሆናል፣

9.3 ቅሬታዉ ሲጣራ የተለዩ ጭብጦች፣ የተደረሰባቸዉን ግኝቶች፣ የመረጃዎችን ምንጮች፣ የተመለከታቸዉን ዝርዝር ማስረጃዎች ፣አስቀርቦ የጠየቃቸዉ/ ያነጋገራቸዉን/ሰዎች አስተያዮች ቀምሮ የዉሳኔ ሀሳብ ለሃላፊ ያቀርባል፣

9.4 የቀረበዉ ቅሬታ በሙሉ ወይም በከፊል ተቀባይነት ያገኘ ወይም ያላገኘ መሆኑን ውሳኔ በተሰጠበት ቀን መረጃዎች ይይዛል ፣

9.5 በቅሬታ ማጣራትና ዉሳኔ ሀሳብ አሰጣጥ ሂደት በቡድኑ መካከል ልዩነት ካለ ከዉሳኔ ሀሳቡ ጋር ለሃላፊ ማቅረብ፣

9.6 የቅሬታ አጣሪ ቡድን አባላት የታክስ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መሰረት አድርገው የውሳኔ አስተያየት ለኃላፊ የሚቀርቡ ሲሆን ለሚያቀርቡት የውሳኔ ሀሳብ የግል እና የቡድን ተጠያቂነት አለባቸው። ጥፋት ፈጽመው ሲገኙም በተቋሙ የሰው ኃይል መተዳደሪያ ደንብ እና በሌሎች ህጎች የሚጠየቁ ይሆናል።

10. የቅሬታ አቅራቢ ግዴታዎች፣

10.1 በታክስ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ታክስ ከፋይ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ዓ.ም አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 34 በፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ)፣ (ሠ)፣ (ረ)፣ (ሰ)፣ ወይም (ሸ) በተመለከቱ ድንጋጌዎች እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 የተመለከተዉን ግዴታዎች ከሚላ በታክስ ዉሳኔዎች ላይ ቅሬታዎች ማቅረብ ይችላል

10.2 የታክስ ዉሳኔ ቅሬታ ስሌት በመለወጥ ፣ በመቀነስ ወይም በዚህ ላይ በተደረገ ማሻሻያ ላይ ከሆነ በመጀመሪያዉ የቅሬታ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፣

10.3 በታክስ ዉሳኔ ቅሬታ ሊያቀርብ የሚችለዉ ባለተስማማበት የታክስ ስሌት ማሰታወቂያ ላይ መሆኑን ተገንዝቦ ማቅረብ አለበት ፤

10.4 በታክስ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ታክስ ከፋይ ቅሬታዉን ማቅረብ ያለበት በጽሁፍ ሲሆን በታክስ አዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹትን መሰረት አድረጎ መሆን አለበት፣

10.5 ታክስ ከፋዩ ቅሬታ አቅርቦ ባቀረበዉ ቅሬታ ላይ በየደረጃው ዉሳኔ ተሰጥቶት ካልተስማማ ይግባኝ ሊጠይቅ የሚችለዉ በክርክር ላይ ያለውን ወለድና ቅጣትን ሳይጨምር 50% /ሀምሳ ፐርሰንት/ ከከፈለ ብቻ በኋላ መሆኑን ማወቅ አለበት፣

10.6 ቅሬታ አቅራቢዉ ባቀረበዉ ቅሬታ ላይ የቅሬታ አጣሪ ቡድኑ ቅሬታዉን እንዲያስረዳ ወይም ተጨማሪ ማስረጃዎች ካሉት እንዲያቀርብ ሲጠይቅ የማቅረብ ወይም የማስረዳት ሀላፊነት አለበት

11. በየደረጃው የሚገኙ የገቢ ተቋም ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት

11.1 ቅሬታ አቅራቢዎች ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ለማቅረብ ከአቅም በላይ በሆነ ምክኒያት ካቻሉና ኃለፊው ካመነበት በአንቀጽ 7.3 ከተቀመጠው በተጨማሪ መረጃውን እንዲያቀርቡ እስከ 5 ቀን ሊፈቀድ ይችላል።

11.2 በቅሬታ አጣሪ ቡድን ለኃላፊዉ የቀረቡ የቅሬታ የውሳኔ ሀሳቦች በበቂ መረጃዎች እንደገና ታይተዉ መቅረብ አለባቸዉ ብሎ ሲያምንበት ከታክስ ህጉ አንፃር ያልታዩ ጉዳዮችን በዝርዝር በማስቀመጥ በድጋሚ የዉሳኔ ሀሳብ እንዲቀርብለት ለቅሬታ አጣሪ ቡድኑ ሊያዝ ይችላል።

11.3 በቅሬታ አጣሪ ቡድን የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ከታክስ ህጉ አንፃር የቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ በወቅቱ ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፣

11.4 በየደረጃው በሚገኝ የአስተዳደር እርከን ያለ ገቢ ተቋም ከላይ ወደታች የሚሰጡ ውሳኔዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት።

11.5 በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 11.4 የተገለጸው ቢኖርም በተሰጠው የቅሬታ ውሳኔ ከታክስ ህጉ አንፃር ተገቢ አይደለም ብሎ ሲያምን ውሳኔውን ለሰጠው አካል ማብራሪያ ጠይቆ በሚሰጠው ምላሽ መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል።

12. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸዉ ህጎች፣

ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረዉ የግብር አቤቱታን የመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር ገባ/3/2001 ዓ.ም እና የታክስ አቤቱታን መርምሮ ለመወሰን የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር፤ ደአ-02/2006 ዓ.ም በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

13. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የታክስ ቅሬታ ለማጣራት ለኃላፊ በሚያቀርቡና ውሳኔ በሚሰጡ እንዲሁም ቅሬታ በሚያቀርቡ ደንበኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

14. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመዉጣቱ በፊት የቀረቡና ዉሳኔ ያላገኙ ቅሬታዎች በዚህ መመሪያ መሰረት ዉሳኔ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

15.ስለ አባሪዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዘው የሚገኙ ሰንጠረዦች ወይም ቅጻቅጾች የዚህ መመሪያ አካል ሆነው እንደ አግባብነታቸው እየተሞሉ ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል።

16. መመሪያዉ የሚፀናበት ቀን

1/ ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በገቢዎች ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ወ/ሮ ብዙአየሁ ቢያዝን

የአማራ ክልል ገቢዎች ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር

2011 ዓ.ም

ባህር ዳር

1. <u>የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን የዉሳኔ ሀሳብ ማቅረቢያና የኃላፊ የዉሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ</u>

1. የቅሬታ አቅራቢዉ/ዋ/ ስም ----------
2. የንግድ ዓይነት----------
3. የግብር ከፋይነት ደረጃ---------- ፋይል ቁጥር _____
4. ቅሬታዉ የቀረበበት ምክንያት √ ይደረግ

4.1 በኦዲት ዉጤት ባለመስማማት ☐

4.2 በቀን ገቢ ጥናት ዉሳኔ ☐

4.3 በግብይት መረጃ ☐

4.4 በሌላ ከሆነ ይገለጽ----------

5. ቅሬታ የቀረበበት ግብር ዘመን----------
6. ቅሬታ የቀረበበት

6.1 ፍሬ ግብር ብር _____

6.2 ታክስ ብር ብር _____

6.3 አገልግሎት ብር ብር _____

6.4 ሌላብር _____

ግብር ከፋዩ ቅሬታ ያቀረበበት ምክንያት ባጭሩ	የቅሬታ ስሚ ቡድን ዉሳኔ ሀሳብ ባጭሩ

7. <u>የአቤቱታ አጣሪ ቡድን አባላት</u> <u>ፊርማ</u> <u>ቀን</u>

7.1 ---------- ---------- ----------

7.2 ---------- ---------- ----------

7.3 ---------- ---------- ----------

8. የሀላፊዉ ዉሳኔ ባጭሩ _____

_____

9. የኃላፊዉ ስም ---------- ፊርማ---------- ቀን ----------
10. ግብር ከፋዩ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሰጠዉ አስተያየት/በመስማማት /ባለመስማማት/ _____

_____

_____

11. ስም ---------- ፊርማ---------- ቀን ----------